47290.doc

40947.doc

41327.doc

41474.doc

42021.doc

42874.doc

42923.doc

43290.doc

43362.doc

43410.doc

የሰበር መ/ቁ 47290

ህዳር 02 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች:-** 1. ሐጎስ ወልዱ

2. ሂሩት መለሰ

3. ታፈሰ ይርጋ

4. አልማው ወሌ

5. ዓሊ መሐመድ

**አመልካች:-** ወ/ሮ ወይንሸት ብርሃኑ - ቀረቡ

**ተጠሪ:-** አልነጃህ ሪሊፍ ሪሃብሊቴሽን ኤንድ ዴቨሎፕመኒት ኦርጋናይዜሽን ባለአደራ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ተተኪ የግብርናና ገጠር ልማት ሚ/ር - አልቀረበም

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ድርጅት በመፍረሱ ምክንያት ከስራ ስለተሰናበቱ በአዋጁ መሰረት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ቀርቦ ከተከራከረ በኋላ ፍ/ቤቱ አመልካች የስራ ስንብት ክፍያና የካሳ ክፍያ እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ ሲጠቃለል በስር ፍ/ቤት ባቀረቧቸው የዳኝነት ጥያቄዎች ላይ ፍ/ቤቱ ሳይወስን ማለፉ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡ ችሎቱም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡

አመልካች የተለያዩ የዳኝነት ጥያቄ አንስተው የስር ፍ/ቤት ያለፈባቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5(3) ዳኝነት ተጠይቆበት ውሳኔ ሳይሰጥ የታለፈ ከሆነ እንደተከለከለ እንደሚቆጠር መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች በሥር ፍ/ቤት ጠይቀው ያልተወሰኑላቸው ጥያቄዎች ውድቅ እንደተደረጉ ይቆጠራሉ፡፡ ስለሆነም ጥያቄዎቹ ውድቅ መደረጋቸው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

አመልካች በአ/ቁ 377/1996 አንቀፅ 40(4)(ሀ) መሰረት ካሳ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ከስራ የተሰናበቱት ድርጅቱ በመዘጋቱ መሆኑ አከራካሪ አልሆነም፡፡ ሆኖም በተጠቀሰው የአዋጁ ድንጋጌ መሰረት ካሳ የሚከፈለው አሰሪው ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ሰራተኛውን ከስራ አሰናብቶ ሲገኝ ነው፡፡ አመልካች ከስራ የተሰናበቱት ግን ድርጅቱ በመዘጋቱ እንጂ በአሰሪው ጥፋት ባለመሆኑ የጠየቁት የካሳ ክፍያ የሚገባቸው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በሌላ በኩል ግን የስር ፍ/ቤት በአዋጁ አንቀፅ 40(3) መሰረት ካሳ እንዲከፈላቸው የወሰነ በመሆኑ አመልካች ተጠቃሚ እንጂ መብታቸው ተጎድቷል ማለት ስለማይቻል የጠየቁት የካሳ ክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የአመልካች የስራ ውል የተቋረጠው በተጠሪ አነሳሽነት ሳይሆን በፍትሕ ሚ/ር ትዕዛዝ ስለሆኑ አመልካች ራሳቸው ገልፀው እያለ ድርጅቱ ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ያቀረቡት ቅሬታም አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ ያልተከፈለ የሁለት ወር ደሞዝን አስመልክቶ አመልካች ያቀረቡትን ቅሬታ ስንመለከት ድርጅቱ የተዘጋው ነሐሴ 02 ቀን 2000 ዓ.ም መሆኑን አመልካች በክሳቸው ላይ ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም የስራ ውላቸው የሚቋረጠው ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ የስራ ውላቸው ከተቋረጠ በኋላ ከመስከረም 1 ቀን 2001 እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2001 ዓ.ም ስለሰራሁ ደሞዝ ይከፈለኝ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ክፍያ ለዘገየበት በማለት የጠየቁትን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት አመልካች ንብረት ካስረከቡ በኋላ ክፍያ ጠይቀው ስለመከልከላቸው አለማስረዳታቸውን በማረጋገጥ ስለሆነ ክፍያውን የከለከላቸው በዚህ በኩል የቀረበውም ቅሬታ ተቀባይነት የለውም፡፡ የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ስንመለከት በመሠረቱ የአመት እረፍት በየአመቱ ሊወሰድ የሚገባ ሲሆን ይህ የእረፍት ጊዜ ወደሚቀጥለው አመት ሊተላለፍ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች አዋጁ አስቀምጧል፡፡ ይኸውም ሰራተኛው ሲጠይቅና አሰሪው ሲስማማበት ወይም አሰሪው የስራ ሁኔታ ሲያስገድደው ስለሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 79(2) እና (3) ያመለክታሉ፡፡ በነዚህ ምክንያቶችም ቢሆን የአመት እረፍት የሚተላለፈው ለሁለት አመት ብቻ ስለሆኑ አንቀፅ 79(5) ያመለክታል፡፡ አመልካች የአመት እረፍት ጠይቀው ስለማስተላለፋቸው ወይም በአሰሪው ምክንያት ስለመተላለፉ በዚህ የሰበር ችሎት እንኳን ገልፀው ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ የአንዱን አመት እረፍት 23 ቀናት እረፍት ደግሞ ስለመውሰዳቸው አምነዋል፡፡ ስለሆነም ከጠየቁት የ4 አመት እረፍት ውስጥ ሁለት አመት ያለፈው ፈቃድ የተቃጠለ በመሆኑ፣ የሶስተኛውን አመት ፈቃድ ደግሞ ስለመተላለፋቸው ያቀረቡት ክርክር ስለሌለ የሶስት አመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በሌሳ በኩል አመልካች ደሞዛቸው ብር 3,200 በመሆኑ የስንብት ክፍያው ሊሰላ የሚገባው በዚሁ መሰረት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ነገር ግን በስር ፍ/ቤት ክስ ሲመሰርቱ ደሞዛቸው ብር 3,200 ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ ምንም እንኳን በማስረጃ መግለጫ ላይ ደሞዛቸው ብር 3,200 ስመሆኑ ማስረጃ ያቀረቡ መሆኑን ቢገልፁም የተያያዘው ግን ደሞዛቸው ብር 2,800 መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የስንብት ክፍያ በብር 2,800 ታስቦ እንዲከፈል በመወሰኑ ስህተት አለመፈፀሙን ተገንዝበናል፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ማለት አልተቻለም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 51027 ሚያዚያ 01 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 80312 ሰኔ 10 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳና ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. የስር ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 40947

ህዳር 15 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች:- 1. መንበረፀሃይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. ታፈሰ ይርጋ

5. አልማው ወሌ

**አመልካች:-** አቶ መዝገቡ መድህኔ - ጠ/ሐጎስ ደበሱ ቀረቡ

**ተጠሪ:-** የአ.አ ከተማ አስተዳደር - ነ/ፈጅ አትርሣው ወልዴ ቀረቡ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች ተጠሪ ሳወጣው ጨረታ ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ብር 20,000 ሊመለስ አይገባም ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው:: አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ባወጣው የጨረታ ብር 2,000,000 የሚያወጡ 32 አይነት እቃዎች ለማቅረብ የተወዳደሩ ቢሆንም ያሸነፉት በሁለት አይነት እቃዎች ብቻ በመሆኑ ውል እንዲሞሉ የቀረበላቸውን ጥያቄ ባለመቀበላቸው ተጠሪ ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ አልመልስም በማለቱ ገንዘቡን እንዲመልስላቸው ጠይቀዋል:: ተጠሪም ለክሱ በሰጠው መልስ አመልካች ባሸነፋባቸው ሁለት አይነት እቃዎች ውል እስካልፈረሙ ድረስ ገንዘቡ ሊመለስላቸው እንደማይገባ ተከራክሯል:: ፍ/ቤቱም አመልካች በዋስትና ሰነዱ ላይ የተመለከተውን ግዴታ እስካልተወጡ ድረስ ገንዘቡ ሊመለስላቸው አይገባም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል:: በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው የነበረ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቶባቸዋል:: የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው:: የሰበር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉም ግራ ቀኙ ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሰምቷል:: መዝገቡም እንደሚከተለው ተመርምሯል::

ተጠሪ ባወጣው የጨረታ ማስታወቂያ አመልካች 32 አይነት እቃዎች ለማቅረብ ተወዳድረው ለጨረታ ማስከበሪያም የእነዚህ እቃዎች ዋጋ አንድ በመቶ ማስያዛቸውን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል:: አመልካች የተወዳደሩበት የጠቅላላ ንብረቶቹ ዋጋ ብር 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን) ስለሆነ የተያዘው ገንዘብ ብር 20,000 ስለመሆኑና አመልካች ከተወዳደሩበት 32

አይነት እቃዎች ውስጥ ያሸነፉት በሁለት እቃዎች ብቻ ስመሆኑ ግራ ቀኙ አልተካካዱም፡፡ አከራካሪው ጉዳይ አመልካች ሳሸነፉበት ሁለት እቃዎች ውል አለመፈረማቸው ያስያዙት ብር 20,000 እንዳይመለስላቸው ይከለክላል ወይስ አይከለክልም የሚለው ነው፡፡

የጨረታ ማስከበሪያ ማለት አንድ ተጫራች ጨረታውን ቢያሸንፍ ውል የሚፈፅም ስመሆኑ ዋስትና እንዲሆን የሚያዝ ገንዘብ ነው፡፡ ስውል መፈፀም ዋስትና ሲባል የሚያዝ ገንዘብ እንደመሆኑም መጠን የጨረታው አሸናፊ ባሸነፈው መሰረት ውል ካልፈረመ የጨረታው ማስከበሪያ ይያዝበታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ብር 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን) ስሚያወጡ 32 ዓይነት እቃዎች ተጫርተዋል፡፡ ስጨረታ ማስከበሪያም የተጫረቱባቸውን ጠቅላላ እቃዎች ዋጋ አንድ በመቶ ብር 20,000 (ሃያ ሺህ) አስይዘዋል፡፡ ከክርክሩ ሂደትም አመልካች ከተወዳደሩባቸው እቃዎች ውስጥ ያሸነፉት በሁለቱ እቃዎች ብቻ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ተጠይቀውም ውል ስመፈረም ፈቃደኛ ያልሆኑት እነዚህን ሁለት እቃዎች በተመለከተ ነው፡፡ አመልካች 20,000 ብር የጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት ጠቅላላ ስተጫረቱበት እቃዎች በመሆኑ ጠቅላላው የጨረታ ገንዘብ ሊያዝ የሚገባው አመልካች በተወዳደሩባቸው እቃዎች በሙሉ አሸናፊ ቢሆኑና በዚሁ መሰረት ውል አልፈርምም ቢሉ ነበር፡፡ አመልካች ያሸነፉት ግን በሁለት እቃዎች በመሆኑ ስነዚህ እቃዎች ውል ስመፈረም ፈቃደኛ ባስመሆናቸው የጨረታው ማስከበሪያ ሊያዝ የሚገባው አሸናፊ በሆኑባቸው እቃዎች ዋጋ መጠን የተያዘው ገንዘብ እንጂ አመልካች ስ32 አይነት እቃዎች ሳስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ በጠቅላላ ሲሆን አይገባብ ባላሸነፉባቸው ዕቃዎች ቀድሞውንም ውል ስመዋዋል ስስማይችሉ ስነዚህ እቃዎች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ ውል አልፈፀሙም ተብሎ ሊያዝባቸው የሚገባበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ሳሸነፉት ሁለት አይነት እቃዎች ውል አልፈረሙም በሚል ስ32 አይነት እቃዎች ያስያዙት ብር 20,000 በሙሉ ሊያዝ ይገባል በሚል የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01619 ጥቅምት 25 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 43929 ሐምሌ 15 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ስ32 ዓይነት እቃዎች ካስያዙት ብር 20,000 ሊያዝባቸው የሚገባው ጨረታ ያሸነፉባቸው ሁለት እቃዎች ዋጋ አንድ በመቶ ብቻ ስስሆነ ይኸው ገንዘብ ተቀንሶ ቀሪው ገንዘብ እንዲመለስላቸው ብለናል፡፡

3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 41327

ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ጋሹ ሰይድ ጠበቃ አቶ ሙላት ፈለቀ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ሽኩር አህመድን አልቀረቡም

2. የፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ

ነገረ ፈጅ አቶ አያሌው በላይ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና በይግባኝ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ህዳር 21 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አንደኛ ተጠሪ በከሳሽነት ቀርቦ የአሁን አመልካች ንብረት የመለያ ቁጥሩ 3-00810 መኪና ሁለት ሺ ኩንታል የበቆሎ ዱቄትና ፋፋ ከናዝሬት ገድሉስቦ የተባለ ቦታ ድረስ እንዲያጓጉዝልኝ ውል ተዋውዬ ቅድሚያ ክፍያ ከፍየዋለሁ፡፡ ተከሳሹ (አንደኛ ተጠሪ) ዱቄቱን ለጉድሉስቦ ጣቢያ አላደረሰም፡፡ በዚህ ምክንያት አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የሚከፈለኝ 37688.62 (ሰላሣ ሰባት ሺ ስድስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ከስልሣ ሁለት ሣንቲም) ያልከፈለኝ ስለሆነ ይህንን ገንዘብ ከህጋዊ

ወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ነው። አንደኛ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርበው እህሉን ለማጓጓዝ ከአመልካች ጋር ውል የተዋዋሉ መሆኑን አምነው እህሉን በማጓጉዝበት ጊዜ መኪናው ጭቃ ይዞት መሄድ ስላልቻለ ይህንኑ ለጉሮ ወረዳ አስተዳደር አመልክተን እህሉ ተራግፎ በመጋዘን የተቀመጠና አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን (ሁለተኛ ተጠሪ) የተረከበ በመሆኑ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባልኝ ማስረጃውም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲቀርብልኝ በማለት ተረክበዋል። ፍርድ ቤቱም ሁለተኛ ተጠሪ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ ሁለተኛ ተጠሪ እህሉን የተረከበ መሆኑን የሚያረጋግጥ ቨርባል ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር ልኳል። ፍርድ ቤቱ በአንደኛ ተጠሪ ጥያቄ መሠረት ሁለተኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ሰጥቷል። ሁለተኛ ተጠሪ በጣልቃ ገብነት ባቀረበው ክርክር የአንደኛ ተጠሪ መኪና በጭቃ ተይዞ እህሉን ካራገፈበት ጉሮ ወረዳ እህሉ መድረስ ወደአለበት ጉድሉስቦ ጣቢያ ለማጓጓዝ ብር 3865.41 (ሶስት ሺ ስምንት መቶ ስልሣ አምስት ብር ከአርባ አንድ ሣንቲም) ከፍለናል። ቀሪው 33823.21 (ሰላሣ ሶስት ሺ ስምንት መቶ ሀያ ሶስት ብር ከሀያ አንድ ሣንቲም) በጨረታ ማስከበሪያነት በመያዝ ገቢ አድርገነዋል በማለት ተከራክሯል። የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን ከሰማ በኋላ ሁለተኛ ተጠሪ በጨረታ ማስከበሪያነት ይዠዋለሁ ያለውን ብር 33823.21 ለከሳሽ (ለአንደኛ ተጠሪ) እንዲከፍል። በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበሩት አመልካች ሁለተኛ ተጠሪ እህሉን እስከ ጣቢያ ድረስ ለመጓጓዝ ያወጣውንና ከአንደኛ ተጠሪ ክፍያ የቀነሰውን ብር 3865.41 ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለከሳሽ (አንደኛ ተጠሪ) እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል። አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት የተፈፀመ የህግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የሌለ መሆኑን በመግለፅ ይግባኛቸውን ሠርዞታል።

አመልካች የሥር ፍርድ ቤት ከሳሽ (አንደኛ) ተጠሪ በክሱ ያልጠየቀውን ጉዳይ በዳኝነት አይቶ ሁለተኛ ተጠሪ ከጉሮ ወረዳ እስከ ጉድሉስቦ ጣቢያ ያጓጓዘበትን ገንዘብ እንድከፍል ወስኗል፡፡ በውሉ መሠረት ያልፈፀምኩት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መኪናዩ በጭቃ በመያዙ ሆኖ እያለ ኃላፊነህ መባሌ ተገቢ አይደለም አንደኛ ተጠሪ ስድስት ሺ ብር ቅድሚያ ክፍያ ከፍያለው ያለው ሀሰት ነው በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት መሠረታዊ የህግ ስህተት ሰርቷል በማለት ያመለከተ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው የሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ ያልጠየቀውን ጉዳይ በዳኝነት አይቶ አልወሰነም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሥነ ሥርዓት ሕጉንና የይዘት ሕጉን መሠረት አድርገው የወሰኑ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አንደኛ ተጠሪ አመልካች በገባው ውል መሠረት እህሉን አጓጉዞ ከመድረሻው ባለማድረሡ ምክንያት ብር 37688.62 ጉዳት ደርሶብኛል ከነወለዱ ተከሳሽ (አመልካች) እንዲከፍሉ በማለት በግልፅ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ በማጣራትና ሁለተኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ በማድረግ አመልካች እስከ ጉሮ ወረዳ እህሉን ያጓጓዙና ከዚያ በኂላ ወደ መድረሻው እህሉን ለማጓጓዝ ሁለተኛ ተጠሪ ያወጣው ብር 3865.41 ብቻ መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች በውሉ መሠረት አሟልተው ባለመፈፀማቸው አንደኛው ተጠሪ የደረሰበትን እርግጠኛ ጉዳት ብቻ እንዲተኩ መወሰኑ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 182(2) የሚጥስ ሣይሆን የህጉን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ዳኝነት የሰጠ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች በውሉ መሠረት እህሉን ከመድረሻው ያላደረስኩት ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ማለትም መኪናው በጭቃ ስለተያዘብኝ ነው በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታም የውል ግዴታ

የገባ ሰው ከአቅም በላይ የሆነ ሀይል አጋጥሞታል የሚባልበት መሠረታዊ ሁኔታ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1792 የተደነገጉትን መሠረታዊ ድንጋጌዎች ከግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና ተቀባይነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች ከአንደኛ ተጠሪ የተቀበለውን የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ መጠን አስመልክቶ ክርክር ያቀረበ ቢሆንም የበታች ፍርድ ቤቶች በአንደኛ ተጠሪና በአመልካች መካከል እህሉን ለማጓጓዝ የተደረገውን የአገልግሎት ኪራይ ውል እና የውሉን አፈፃፀም አመልካች የተቀበለውን ገንዘብ መጠን በጭብጥነት በመያዝ ውሣኔ ያልሰጡ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ህጉን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አፅንተነዋል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. አመልካችና ተጠሪዎች በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 41474

ህዳር 1 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ብረታ ብረት ማቅለጫ ፋብሪካ - ጠበቃ ሸዋንግዛው አድማሱ

**ተጠሪ፡-** በቀለ ነጋሽ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.63012 ነሐሴ 18 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ላይ ነው፡፡ ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ተጠሪ ክስ የመሠረተው ተመድቤ እየሠራሁበት ላለው የሥራ መደብ ሊከፈል የሚገባው ክፍያ እንዲሠጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱም ከአመልካች የተሰጠውን መልስ ካየ በኋላ፣ ተጠሪ በቦታው ላይ ሊያገኝ የሚገባውን ደመወዝ ታስቦ ይከፈለው በማት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በጭማሪ ይከፈል የተባለውን ሁለት እርከን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ በማሰብ ከፍሎ በማቆሙ ተጠሪ ይህን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ተጠሪ የሁለት እርከን ጭማሪ በሚያስገኝ የሥራ መደብ ላይ ተመድቦ እየሠራ መሆኑ ተረጋግጦ ጭማሪው እንዲከፈለው የተወሰነለት በመሆኑ እቦታው ላይ እስካለ ድረስ ሊቋረጥ አይችልም

የሚል ምክንያት በመስጠት ክፍያው እንዲቀጥል ወስኖአል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው።

በበኩላችንም አመልካች ህዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የተጠየቀውን ዳኝነት መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ተብሎ ነው። በዚህ መሠረትም ይህ ነጥብ ከግራቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።

በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጡትን ውሳኔዎች ይዘት በዝርዝር ተመልክተናል። የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በውሳኔው በግልጽ ያመለከተው የመጀመሪያው ነጥብ ተጠሪ የተመደበበት ሥራ የሁለት እርከን ጭማሪ የሚያስገኝ እንደሆነ በማስረጃ ማረጋገጡን ነው። በመቀጠልም ህዳር 30 ቀን 97 ዓ.ም እንደመነሻ በመያዝ ከዚህ ቀን ጀምሮ ተጠሪ ጭማሪውን የማግኘት መብት አለው ብሎአል። በመጨረሻም ይኸው ታስቦ እንዲከፈለው ሲል ውሳኔውን አጠቃሎአል። አመልካች በዚህ መልክ የተሰጠውን ውሳኔ በራሱ አስተሳሰብ በመተርጎም ከህዳር 30 ቀን 97 ዓ.ም ጀምሮ ፍ/ቤቱ ውሳኔ እስከሰጠበት ሚያዝያ 15 ቀን 99 ዓ.ም ድረስ ላለው ጊዜ ብቻ አስልቶ በመክፈል አቁሞአል። ተጠሪ ወደይግባኝ የሄደውም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የአመልካችን አስተሳሰብ በመቀበሉ ነው። የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግን አፈጻጸሙ ዋናውን ውሳኔ መሠረት ያላደረገ ነው በማለት አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ሰጥቶአል።

እኛም እንደምናየው ተጠሪ የሁለት እርከን ጭማሪ ባለበት የሥራ መደብ ላይ ተመድቦ እየሠራ መሆኑ ተረጋግጦ ጭማሪው እንዲከፈለው መወሰኑ ተረጋግጦአል።

እዚህ ላይ በዋነኝነት መታየት ያለበት ጭማሪው ይከፈል የተባለው ለቦታው ነው፡፡ ተጠሪ ከቦታው ተነስቶአልም አልተባለም፡፡ በመሆኑም የክፍያው መቀጠል የሚወሰነው በጊዜ ገደብ ሳይሆን፣ ተጠሪ በቦታው ላይ መሥራት ቀጥሎአል ወይስ አልቀጠለም በሚለው ላይ ነው፡፡ ሁኔታው ይህ ከሆነ ደግሞ ክፍያው የሚፈጸመው ፍ/ቤቱ ውሳኔ እስከሰጠበት ጊዜ ድረስ ብቻ ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ከዚህ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚባል አይደለም፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 63012 ነሐሴ 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቶአል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሠ/መ/ቁ 42021

ህዳር 01 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ባዩሽ መኩሪያ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ብርቂ ቶላ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአፈፃፀም ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በዲገሉና ጢዮ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኗ አመልካች በከፈቱት የአፈፃጸም አቤቱታ ነው፡፡ አመልካች ለአፈፃጸም መሰረት ያደረጉት በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 07495 የሠጠውን የመጨረሻ ውሳኔ ሲሆን የአሁኗ ተጠሪ በአፈጻጸም ተከሳሽነት ቀርበው ተገቢ ነው የሚሉትን ክርክር አቅርበው ከተከራከሩ በኋላ አፈፃጸሙን የያዘው ፍርድ ቤትም ሆነ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ቤት የተጠሪ ክርክር በዋናው ክርክር ጊዜ ሊታይ ይችል የነበረው እንጂ በአፈፃጸም ወቅት ሊነሣ የሚችል አይደለም በማለት በውሳኔው መሠረት እንዲፈፅሙ ትዕዛዝ ሠጥተዋል፡፡ ተጠሪ በዚህ ትእዛዝ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ እና ይኸው ፍርድ ቤት ተገቢውን ማጣራት ካደረገ በኋላ ለአፈፃጸሙ መሰረት የሆነው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት መወረሱንና በዋና ክርክር ወቅትም ውሳኔ ያላረፈበት መሆኑ ተረጋግጧል በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን የአፈፃጸም ትእዛዝ ሽሯል፡፡ በጉዳዩ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በሚል ምክንያት አመልካች አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት አቀርበውም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በአፈፃጸም ክርክር ላይ የተሠጠውን ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ታህሳስ 13 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሣኔ በዋናው ጉዳይ ላይ የተሠጠውን የፍርድ ይዘትን ያላገናዘበ እና ከሚመለከታቸው አካላት ቀረበ የተባለ ማረጋገጫም ሐሰተኛ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሠጠው አይገባውም በማለት መከራከራቸውን እና በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ ተሽሮ አፈፃጸሙ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ቤት እንዲቀጥል ውሣኔ እንዲሰጣቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል የሚል ትዕዛዝ ተሠጥቶ የግራ ቀኙ ክርክር ግንቦት 26 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሠምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሠበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው ነጥብ ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የተመለከቱትን የአፈፃፀም ክርክር የሚመራባቸውን ድንጋጌዎችን ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በዋናው መዝገብ ላይ ተጠሪ ቁጥሩ 515-01 በሚለው መኖሪያ ቤት አካል በሆነው ክፍል ላይ ሁከት ፈጥራለች፣ ቤቱን እንድትለቅ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀው የተወሰነላቸው መሆኑንና ይኸው ውሳኔ እንዲፈፀምላቸው የአፈፃፀም አቤቱታ ሲያቀርቡ ተጠሪ ቀርበው ለአፈፃፀሙ መሰረት የሆነው የቤት ቁጥር 514–01 መሆኑንና ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ ያልተሠጠበትና መንግስት ወርሶት ተጠሪ ተከራይተውት የሚገኙበት መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ይህንኑ የተጠሪን ክርክር የስር ፍርድ ቤቶች በዋና ክርክር ጊዜ ይታይ ይገባው የነበረ መሆኑን ጠቅሰው የተጠሪን አቤቱታ ውድቅ ያደረጉ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግን ከሚመለከታቸው አካላት ተገቢው መግለጫ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ ሠጥቶ ትዕዛዙ የተላለፈላቸው አካላትም ለአፈፃፀሙ መሰረት የሆነው የቤት ቁጥር 514-01 ከቤት ቁጥር 515-01 የተለየ በመንግስት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ተወርሶ ቀበሌው እያስተዳደረው ለተጠሪ ተከራይቶ የሚገኝ መሆኑን በመግለፅ ማስረጃ

አቀርበዋል፡፡ አመልካች ይህን ማስረጃ ሀሰተኛ በማለት የሚከራከሩ መሆኑንም ተመልክተናል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በግልፅ የሚያሳየው ለአፈፃፀሙ መሰረት የሆነው ጉዳይ በማስረጃ ተጣርቶ ውሳኔ ያረፈበት መሆኑን ነው፡፡ የቀረበው ማስረጃ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሳኔ ያረፈበት የቤት ቁጥርና በአፈፃፀም አመልካች የገለፁት የቤት ቁጥር የተለያየ መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡ አንድ የአፈፃፀም ማመልከቻ ደግሞ መሰረት ማድረግ ያለበት በዋናው ጉዳይ ላይ የተሠጠውን ውሳኔ መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በዋናው ክርክር ውሳኔ ያላረፈበት ጉዳይ ለአፈፃፀም መሰረት ሊሆን የሚችልበት የህግ መሰረት የለም፡፡ በመሆኑም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ውስጥ ስለአፈፃፀም የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ እንጂ ድንጋጌዎቹን የሚፃረር አይደለም፡፡ አመልካች በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ሀሰተኛ ናቸው በማለት ያቀረቡት ክርክር ደግሞ ይህ ችሎት ማስረጃ የመመዘን ሕጋዊ ሥልጣን ስለሌለው ሊስተናገድ የሚገባው አይደለም፡፡ ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 34645 ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በዚሁ ፍርድ ቤት ሠበር ችሎት በመ/ቁጥር 61933 ሠኔ 30 ቀን 2000 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 42874

ህዳር 29 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች:- ሐጐስ ወልዱ**

**ሂሩት መለሰ**

**ታፈሰ ይርጋ**

**አልማው ወሌ**

**ዓሊ መሐመድ**

**አመልካች:- ካሣዬ ኃ/ማርያም ቀረበ**

**ተጠሪ:- ወ/ሮ እጅጋየሁ ገርቢ ወኪል ደረጀ ገርቢ ቀረበ**

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጋብቻን በፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተነሣውን የንብረት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ክርክሩ በተጀመረበት የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ በምዕራብ ሸዋ ዞን የባኮ ትቤ ወረዳ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው አመልካች ነው፡፡ ባቀረበው ክስም ፍ/ቤቱ የባልና የሚስቱ የጋራና የግል የሆኑ ንብረቶች በመለየት አከፋፍሎ ድርሻውን እንዲሰጠው ጠይቆአል፡፡ በእሱ እምነት የጋራ የሆኑ እና የጋራ ያልሆኑ (የእሱ የግል የሆኑ) ንብረቶች ዝርዝርም አቅርቦአል፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጠችው መልስ የበኩልዋን ክርክር አቀርባለች፡፡ አመልካች የግል ንብረቴ ነው በማለት በክስ ማመልከቻው የጠቀሰው ንብረት ቀደም ሲል በተደረገው የእርቅ ስምምነት እና ውል መሠረት የጋራ ሃብት ተደርጎአል በማለትም ተከራክራለች፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ በንብረት ክፍፍሉ ሳይ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን፣ አመልካች የግል ንብረቴ ነው ያለው በባኮ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ ይገኛል የተባለው ቁጥር 436 የሆነው ቤት አመልካች ከጋብቻው በፊት በግዢ ያገኘው የግል ንብረቱ ነው ብሎአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ የነበረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም የበኩሉን ክርክር ከሰማ በኋላ ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ አፅንቶአል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ደግሞ አመልካች በራሱ ፍላጎትና ስምምነት ቤቱ የጋራ ሀብት እንዲሆን ያደረገው ስለሆነ የባልና ሚስቱ የጋራ ነው በማለት ወስኖአል፡፡ የጠ/ፍ/ቤቱ የሰበር ችሎትም ይህ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት አመልካች ያቀረበለትን አቤቱታ ውድቅ አድርጎአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ሳይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥር 19 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው ተጋቢ ወገኖች በትዳር በሚኖሩበት ጊዜ የሚያደርጉዋቸው ውሎች ፍ/ቤት ካላፀደቃቸው ውጤት አይኖራቸውም የሚለው የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 89 በሥር ፍ/ቤቶች የታየበትን አግባብ ከመመርመር አኳያ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ግራቀኝ ወገኖች ያላቸውን ክርክር ያሰሙ ሲሆን፣ በበኩላችንም ክርክሩን አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው አከራካሪው ቤት ከጋብቻው መመሥረት በፊት አመልካች ከአንድ ግለሰብ በመግዛቱ ነው የግል ንብረቴ ነው የሚል ክርክር ሲያነሳበት የቻለው፡፡ ተጠሪ ደግሞ ለክርክርዋ መሠረት ያደረገችው ቤቱ የተገዛበትን ጊዜ ሳይሆን፣ የጋብቻውን መመስረት ተከትሎ በተደረገው የጋብቻ ውል ወይም ስምምነት የጋራ ሆኖአል የሚለው ነው፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ያየው የወረዳ ፍ/ቤት ቤቱ የአመልካች የግል ንብረት ነው ለማለት የቻለው ጋብቻው ከመመስረቱ በፊት የተገኘ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ሲሆን፣ የከፍተኛው ፍ/ቤትም ተመሣሣይ ምክንያት በመስጠት ውሳኔውን ያፀናው ሌላው ከክርክሩ አመጣጥ የተገነዘብነው አመልካችም ቢሆን አሁን ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው አቤቱታ በመከራከሪያነት ያነሳው ውሉ በፍ/ቤት አልፀደቀም የሚለው ነጥብ በሥር ፍ/ቤቶች በተደረገው ክርክር አለማንሳቱን ሲሆን፣ ተጠሪ ግን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ቤቱ የጋራ ሃብት የሆነው በመሃከላችን በተደረገው ስምምነት መሠረት ነው የሚል ወጥ የሆነ ክርክር አቅርባለች፡፡ በመጨረሻ ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ቤቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት ነው ለማለት የበቃው በሁለቱ ወገኖች መካከል የተደረገው ውል በሽማግሌዎች ፊት ከመደረጉም በላይ፣ በፍ/ቤትም ተረጋግጦአል የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነም ከውሳኔው ይዘት አረጋግጠናል፡፡

እንደምንመለከተው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ቤቱን በተመለከተ ስምምነት ስለመደረጉ አላከራከረም፡፡ አመልካችም ከሥር ጀምሮ ሲከራከር የነበረው (የመጣው) የተደረገ ስምምነት የለም በማለት ሳይሆን፣ ቤቱ ጋብቻው ከመመስረቱ ቀደም ብሎ በግሌ የገዛሁት ነው የሚል ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ውሉ በፍ/ቤት አልፀደቀም የሚለው የመከራከሪያ ነጥብ በሥር ፍ/ቤቶች አለማንሳቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የጠ/ፍ/ቤቱ በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክርም በማየት ውሉ በፍ/ቤት የተረጋገጠ መሆኑን ገልጾ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ በዚህ አይነት በማስረጃ ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ ፍሬ ነገርን መሠረት ያደረገ ከመሆን አልፎ የሕግ አተረጓጎምን የሚመለከት አይደለም፡፡

የሰበር ችሎቱ በሥር ፍ/ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠባቸው ጉዳዮች በሰበር ሥልጣኑ ማየትና መወሰን የሚችለው በሕግ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ እንደሆነ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት 80(3)(ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁ 25/88 አንቀጽ 10 በግልጽ ተደንግጎአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ያቀረበው ክርክር የአንድን ፍሬ ነገር በማስረጃ መረጋገጥ አለመረጋገጥ የሚመለከት ሲሆን፣ በዚህ ክርክር ላይ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን ያለው የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ፍሬ ነገሩን በማስረጃ አረጋግጦ ወስኖአል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ሰበር ችሎት የሚመረመር የሕግ አተረጓጎም ስህተት የለም ብለናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 49374 ታህሳስ 14 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የጠ/ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎት በሰበር መ.ቁ 70644 ታሕሣሥ 23 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ፀንተዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሬ/ታ

የሰበር መ/ቁ 42923

ህዳር 22 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. ታፈሰ ይርጋ

5. አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ነጻት አባስ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996ን መሰረት ያደረገ የደመወዝ ማስተካከያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ናቸው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘት፣ የሁለት ዓመት የሥራ ልምድ የሚጠይቅ በሙሉ ስታትስቲሺያን የሥራ መደብ ተቀጥረው በወር ብር 1971.00 (አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አንድ ብር) ደመወዝ እየተከፈላቸው በመስራት ላይ የሚገኙ መሆኑን፣ አነስተኛ የሥራ ልምድ ያላቸው እና ተመሳሳይ ስራ የሚሰሩ ሌሎች ሠራተኞች ከፍ ያለ ደመወዝ እንደሚከፈላቸው ገልፀው ድርጊቱ ለአንድ ሥራ እኩል ክፍያ የሚለውን መርህ የሚጥስ በመሆኑ አመልካች የወር ደመወዙን ብር 2366.00(ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ስልሳ ስድስት ብር) እንዲያደርግላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካችም በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሠጠው መልስ ተጠሪ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑንና ጥያቄአቸውም በይርጋ የታገደ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት፣ በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ የደመወዝ ልዩነት የተደረገው መመሪያውን መሰረት በማድረግ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 14(1/ረ) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በዋቢነት በመጥቀስ የአመልካች አሰራር ህገ ወጥ ነው በማለት ለተጠሪ የደመወዝ ማስተካከያ በማድረግ በፔሮል ላይ ሊተክል ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ

የቀረበለት ፍርድ ቤትም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ሠርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥር 19 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የስር ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የአዋጅ ቁጥር 337/96 አንቀፅ 14(1/ረ) አሰሪው መመሪያውን መሰረት በማድረግ ለፈፀመው ተግባር አግባብነት የሌለው በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የስር ፍርድ ቤት አመልካች መስሪያ ቤት ከዘረጋው የእድገት አሰጣጥ ሥርዓት አልፎ ለተጠሪ የወሰነው የደመወዝ መጠን መነሻን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ ጉዳዩ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ሐምሌ 22 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በተመሳሳይ ደረጃ በሚገኙ ሠራተኞች መካከል የሚፈጠር የደመወዝ ልዩነት (Equal Pay Discrimination) የተከለከለ ነው የሚለውንና ኢትዮጵያ ያፀደቀችውን ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽንን መሰረት ያደረገ ስለሆነ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለውም በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩላቸው ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ ሊመረመር ይገባዋል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በስታትስቲሽያንነት ተቀጥረው የሚሰሩ መሆኑን፣ ቅጥሩም በሙሉ ስታትስቲሽያን የስራ የማዕረግ መፈፀሙን በተጠሪና በሌሎች ሠራተኞች መካከል የደመወዝ ልዩነት የተፈጠረው እነዚህ ሠራተኞች ምንም የስራ ልምድ በማይጠይቅ በመለስተኛ ስታትሺያን የስራ መደብ ተቀጥረው ከቆዩ በኋላ በዚህ የስራ መደብ የተቀጠሩ የዲግሪ ምሩቃን ሰራተኞች ወደሚቀጥለው የስራ መደብ የሚያድጉበትን ሁኔታ አመልካች በመመሪያ መወሰኑንና በዚህ መመሪያ መሰረትም ከተጠሪ ጋር ተመሳሳይ ስራ የሚሰሩ የዲግሪ ምሩቃን ከተጠሪ የተለየ ደመወዝ የሚከፈላቸው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 42(1/መ) ድንጋጌ የሚያሳይ ሲሆን ኢትዮጵያ የተቀበለችው አለም አቀፍ ኮንቬንሽንም ይህንኑ ያስገነዝባል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ሲያደርግ መሰረት ያደረገው የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14(1/ረ) ሲሆን የዚህ ድንጋጌ ይዘት ሲታይ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣ በሐይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት እና በሌሎችም ሁኔታ በሠራተኞች መካከል ልዩነት ማድረግ ለማንኛውም አሠሪ ሕገወጥ ድርጊት ነው የሚል ነው፡፡ የድንጋጌው እንግሊዘኛ ትርጉሙም "discriminate between workers on the basis of nationality, sex, religion, political outlook, or any other conditions shall be unlawful for an employer." በሚል ተቀምጧል፡፡

ከድንጋጌው ውስጥ "…በሌሎችም ሁኔታ…" ወይም "…. Any other conditions…." የሚለው ሐረግ ጠቅላላ ቃል መሆኑ ግልጽ ሲሆን እንዲህ በሆነ ጊዜ ቃሉን ህግ አውጪው የተጠቀመው ምንን ለማመላከት ነው የሚለው ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ሲሆን የህግ አተረጓጎም መርሆዎችን መሰረት በማድረግም ምላሹን ማግኘት ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት ከጠቅላላው ቃል በፊት የተዘረዘሩት የቃልት ዝርያ የሚያሳዩትን ሁኔታ በመመልከት ጠቅላላ ቃል ሌሎች ያልተዘረዘሩትን ተመሳሳይ ዝርያ ያላቸውን ቃላት ለመጠቀም ታስቦ የተቀመጠ ነው በሚል እንደሚተረጎም ተቀባይነት ያላቸው የህግ አተረጓጎም መርሆዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14(1/ረ) ድንጋጌ ስር "በሌሎች ሁኔታም" የሚለው ቃል ከቃሉ በፊት የተቀመጡትን የልዩነት ማድረጊያ ድርጊቶችን ዓይነት የሚመለከት እንጂ አሰሪው የእድገት አሠጣጥ ሥርዓቱን በመመሪያ ዘርግቶ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ሠራተኞች መስፈርቱን ካላሟሉ ሰራተኞች የተለየ ክፍያ እንዲከፈል የሚያደርግበትን አሰራር የሚመለከት አይደለም፡፡ መመሪያው በሕገ መንግስቱ፣ በዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14(1/ረ) ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ በተጠሪና በሌሎች ሰራተኞች መካከል የደመወዝ ልዩነት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ መመሪያው መድሎን ለመከላከል የማያስችል ነው ሲባል የሚችልበትን ሕጋዊ ምክንያትም አላገኘንም፡፡ ሲጠቃለልም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ከላይ በተመለከቱት ህጋዊ ምክንያቶች መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 23005 ሐምሌ 28 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 70763 ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪና በሌሎች ሠራተኞች መካከል ለተመሳሳይ ሥራ የደመወዝ ልዩነት ያደረገው በሕግ የተከለከሉ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ባለመሆኑ ለተጠሪ ብር 2366.00 በፔሮል እንዲተክል የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ. 43290

ህዳር 15 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች:- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች:-** ወ/ሮ አልማዝ ገ/ሕይወት - ጠበቃ ሙሉጌታ ገብሩ ቀረቡ

**ተጠሪ:-** አቶ ፊልሞን አብርሃ - ጠበቃ ምናስ አስሙ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጋብቻን በፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተነሳውን የንብረት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር አመልካች የጋራ ናቸው የምትላቸውን ንብረቶች በመዘርዘር ድርሻዋን ይሰጣት ዘንድ ጠይቃለች፡፡ ተጠሪም በአንድ በኩል አመልካች ባቀረበችው ክስ መልስ ሲሰጥ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በእሳፊ ወስዳዋለች ያለውን ንብረት በመዘርዘር ከዚሁ ላይ የድርሻውን ያገኝ ዘንድ እንዲወሰንላት ጠይቆአል፡፡ ፍ/ቤቱም ክርክሩን በአንድ ላይ አጠቃሎ ከሰማ በኋላ ተገቢ ነው ብሎ ባመነው መንገድ የንብረት ክፍፍሉ እንዲፈጸም ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በውሳኔው ባለመስማማት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ የነበረ ቢሆንም፣ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው አመልካች የጋራ ነው በማለት ክፍፍል የጠየቀችበት የንግድ መደብር የተጠሪ የግል ንብረት ነው የተባለበትን አግባብ ከመመርመር አንፃር ነው፡፡ ግራቀኙ ወገኖች ይህን መሠረት በማድረግ ክርክራቸ ያሰሙ ሲሆን፣ እኛም በዚህ ረገድ የተሰማው ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በአመልካች የሰበር አቤቱታ እንደተመለከተው ለክርክሩ መነሻ የሆነው የንግድ መደብር በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 2 ቀበሌ 09 ክልል ውስጥ የሚገኝ ንግስተ ሳባ ወርቅ ቤት በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ በተጠሪ በኩል ንግድ ቤቱን በሚመለከት የቀረበው ክርክር ጋብቻው ከመመስረቱ በፊት የተቋቋመ የግል ንብረቴ ነው የሚል ሲሆን አመልካች ደግሞ ጋብቻው ሲመሠረት የጋራ ሃብት እንዲሆን በስምምነታችን ተወስኖአል፡፡ የባልና ሚስት የጋራ ሃብት እንጂ የባልየው የግል ንብረት አይደለም በማለት ነው የምትከራከረው፡፡ ለዚህ ክርክርዋ በአስረጂነት የጠቀሰችውም ጥር 19 ቀን 90 ዓ.ም የተደረገው ውል ነው፡፡

በአስረጂነት የተጠቀሰው ሰነድ በሥር ፍ/ቤቶችም ቀርቦ የተየ ሲሆን፣ ክርክር የተነሳው በይዘቱ ሳይሆን፣ በአተረጓጎሙ ረገድ በመሆኑ በበኩላችንም ሰነዱን ተመልክተናል፡፡ ርእሱ “የሀገር ባህል ጋብቻ ስምምነት” የሚል ሆኖ በመጀመሪያው ፓራግራፍ የተቀመጠው ተጠሪ የገባውን ግዴታ ወይም ያደረገውን ስምምነት ነው፡፡ ይህም ወ/ሪት አልማዝ ገ/ህይወትን (የአሁንዋ አመልካች) የኑሮ ጓደኛው እንድትሆነው ፈቅዶ ሲያገባት ባለው የንግድ ድርጅት ልዩነት በሌለው በፍትሐብሔር ሕግ ቁ 652 መሠረት ጋብቻው የፈጸመ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በአመልካች ይህ አባባል ተጠሪ ንግድ ቤቱን የጋራ ሃብት እንዲሆን መስማማቱን ያመለክታል በሚል የተተረጎመ ሲሆን፣ በተጠሪ አይታ ደግሞ አባባሉ ንግድ ቤቱን የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት እንዲሆን ስምምነት መደረጉን አያሳይም በሚል ተተርጉሞአል፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም የተጠሪውን ክርክር በመቀበል ስምምነት የተደረገው በንግድ ቤቱ ባለሃብትነት ላይ ሳይሆን ከንግድ ቤቱ በሚገኘው ገቢ ላይ ብቻ ነው እሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ በዚህ መሠረትም ንግድ ቤቱ የተጠሪ የግል ሃብት ነው በማለት ወስነዋል፡፡

በበኩላችን እንደተገነዘብነው ሰነዱ “የሃገር ባህል ጋብቻ ስምምነት” የሚል ርእስ የተሰጠው ቢሆንም፤ ይዘቱ ግን ጋብቻውን መፈጸሙን መሠረት በማድረግ የተደረገ የጋብቻ ውል ነው፡፡ ሰነዱ ሲፈረም በዋናነት የተገለጸው አመልካች እና ተጠሪ በየበኩላቸው በንብረት እና በገንዘብ ረገድ ያደረጉትን መዋጮ ነው፡፡ ይኸውም አመልካች የንግድ መደብሩን በመዋጮ ሲያቀረብ ተጠሪ ደግሞ ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ማዋጣትዋ በውሉ ተመልክቶአል፡፡ ውሉ ሲደረግም በአመልካች በኩል ሁለት፤ በተጠሪ በኩልም እንደዚሁ ሁለት በአጠቃላይ አራት ምስክሮች ፈርመዋል፡፡ ይህም በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ.213/92 በአንቀጽ 44 እንደተመለከተው ውሉ በሕግ የሚጠበቀውን ፎርም ያሟላ መሆኑን ያሳያል፡፡ ሰነዱ የጋብቻ ውል መደረጉን ካመለከተ ይዘቱም ከዚህ ውጪ ይሆናል ብሎ ማሰብ የሚቻል አይደለም፡፡ ተጋቢዎች ያደረጉት ስምምነት ግልጽ ነው፡፡ ተጠሪ የተስማማው ከንግድ ቤቱ በሚገኘው ገቢ ላይ

ነው የሚለው በስር ፍ/ቤቶች የተደረሰው ድምዳሜ ከሰነዱ ይዘት የተገኘ ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት በበኩላችን አላገኘንም፡፡ ስለዚህም በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በጋብቻ ውሉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 04035 ታህሳስ 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 64102 ታህሳስ 23 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 2 ቀበሌ 09 ክልል ውስጥ የሚገኝ በቤት ቁጥር 811 የሚታወቀው ንግስተ ሳባ ወርቅ ቤት የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ንብረት ነው ብለን ወስነናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሠ/መ/ቁጥር 43362

ህዳር 30 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. ታፈሰ ይርጋ

5. አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ብሔራዊ ኢንሹራንስ ኩባንያ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኢንሹራንስ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ የመድን ሽፋን በሠጠው መኪና ላይ ጉዳት አድርሷል በተባለው የመኪና ባለንብረትና አሽከርካሪ ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ተጠሪ መድን በሠጠው መኪና ጉዳት አድርሷል ስተባለው መኪና የመድን ሽፋን ሰጪ በመሆኑ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ተጠይቆ ጣልቃ ገብቶ ተከራክሯል፡፡

አመልካች በክርክሩ ገብቶ የደንበኛው መኪና ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ያለመሆኑን፣ በወቅቱ ፕላኑን ያነሳው ትራፊክ ሁለት የአደጋ ቦታዎችን የመዘገበና ይህም አግባብ አለመሆኑን፣ ተጠሪ በደንበኛው ላይ የደረሰው ጉዳት ሙሉ ጉዳት (Total Damage) ነው በማለት በግሉ ከአደጋው በኋላ ከራሱ ደንበኛ ጋር ውል በመፈፀም የከፈለው ገንዘብ አግባብነት የሌለው መሆኑን እንዲህ ከሆነም ጉዳት የደረሰበትን የመኪና አካል ለተጠሪ ማስረከብ ሲገባው በፈለገው ዋጋ መሸጡ አግባብነት የሌለው መሆኑንና ይህ ሁሉ የሚታለፍ ቢሆን እንኳ አመልካች በሰጠው የመድን ሽፋን ልክ ብቻ ኃላፊ እንደሚሆን በመግለፅ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአመልካች ደንበኛ ለጉዳቱ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን በመጥቀስ ተጠሪ ብር 107,853.50 ከእነ ወለዱ ክሱ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ተጠናቆ እስኪከፈል ድረስ በባንክ ሂሳብ ወለድ መሰረት ታስቦ፣ የጠበቃ አበል አስር ፐርሰንት የዳኝነትን ጨምሮ በአመልካች እንዲከፈለው ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ ለኦሮሚያ ጠቅላይ

ፍርድ ቤት በይግባኝ ቀርቦም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የካቲት 03 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የአመልካች ደንበኛ ለጉዳቱ ኃላፊ ናቸው የተባሉት ያላግባብ መሆኑንና አመልካች ከመድን ሽፋን በላይ እንዲከፍል መወሰኑ ስህተት መሆኑን ዘርዝረው መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ከሠጠው የመድን ሽፋን በላይ እንዲከፍል የተሠጠው ውሳኔ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ የተጠሪ ነገረ ፈጅ ነሐሴ 18 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገፅ ማመልከቻ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የመድን ሽፋን መጠኑን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር መሆኑን በመግለፅ የአመልካች ክርክር ውድቅ እንዲሆን የተከራከሩ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም የአመልካች ደንበኛ ለጉዳቱ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍ አለመሆኑን በመዘርዘር መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃም ነሐሴ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የመልስ መልስ ማመልከቻ የመድን ሽፋን መጠኑን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት አንስተው የተከራከሩበት ነጥብ መሆኑን በመግለፅ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ ሊተይ ይገባዋል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች የደንበኛውን ለጉዳቱ ኃላፊነት በተመለከተ ያቀረበው ቅሬታ ከግራ ቀኙ ወገኖች ከቀረበው ማስረጃ አንፃር ታይቶ እና ማስረጃውም ተመዝኖ እልባት ያገኘ ሲሆን ይህ ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶች የሠጡትን ውሳኔ ማረም የሚችለው በሕግ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖሩ ሲረጋገጥ በመሆኑ፣ የአመልካች ቅሬታ በማስረጃ አመዛዘን ረገድ የስር ፍርድ ቤት ስህተት ፈፅሟል የሚል ይዘት ያለው በመሆኑ ይህ ችሎት የሚመረምረው ነጥብ ስላልሆነ ታልፏል፡፡

በዚህ ችሎት ሲታይ የሚገባው የአመልካች የኃላፊነት መጠን ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች የኃላፊነት መጠኑን በስር ፍርድ ቤት ያላነሳው አዲስ ክርክር በመሆኑ በዚህ ችሎት ሲታይ አይገባውም በሚል ተከራክሯል፡፡ ሆኖም አመልካች በደንበኛው ለጉዳቱ ኃላፊነት ላይ ተገቢነት

አሳቸው ያሳቸውን መከራከሪያ ነጥቦችን በማንሳት ከተከራከረ በኋላ ደንበኛው ኃላፊነት አለው የሚባል ቢሆን እንኳ የአመልካች ኃላፊነት በመድን ውሉ ላይ በተጠቀሰው መጠን ብቻ ስለመሆኑ ገልፆ መከራከሩን በስር ፍርድ ቤት በጣልቃ ገብነት ሲከራከር በሰጠው መከላከያ መልስ ማመልከቻ መግለፁን ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር አዲስ ክርክር ነው በማለት ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ወደ ዋናው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ለደንበኛው የሠጠው የመድን ሽፋን ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ ብር) መሆኑን ገልፆ የሚከራከር መሆኑን ተገንዝበናል፤ የመድን ሽፋን ፖሊሲውንም ተመልክተን መጠኑ በአመልካች የተገለፀው መሆኑን አረጋግጠናል፡፡ በመሠረቱ በአመልካች እና በደንበኛው መካከል ያለው ግንኙነት በውል ላይ የተመሰረተ በመሆኑ መድን ሠጪው የሆነው አመልካች ሲገደድ የሚችለው የካሳ መጠን በመድን ውሉ ላይ የተመለከተውን ያህል ነው፡፡ የንግድ ሕግ ቁጥር 665(2) ድንጋጌም ኢንሹራንስ ሰጪው የሚከፍለው ገንዘብ መጠን በውስታው ላይ ከተጠቀሰው አይበልጥም በማለት አስገዳጅነት ባለው ኃይለ ቃል ደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች ኃላፊነት አለበት የተባለው ይህንኑ ድንጋጌ ባላገናዘበ መልኩ በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው መጠን በላይ ሆኖ ስለአገኘነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 11919 ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 66756 ሕዳር 05 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ሊገደድ የሚገባው በመድን ውሉ በገባው ሽፋን መጠን በመሆኑ ለተጠሪ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ከሠጠበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከሚታሰበ 9% (ዘጠኝ በመቶ) ሕጋዊ ወለድ ጋር ይክፈል ብለናል፡፡
3. አመልካች ኃላፊ ነው ተብሎ በዚህ ፍርድ ቤት በተወሰነው መጠን መሰረት ወጪና ኪሳራን በተመለከተ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሠጡት ውሳኔዎች አልተነኩም፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

**ሬ/ታ**

የሰበር መ/ቁ 43410

ህዳር 30 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች:-** 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መሰሰ

4. ታፈሰ ይርጋ

5. አልማው ወሌ

**አመልካች:-** የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ አሠገደች ጎርፌ

**ተጠሪ:-** ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል - አልቀረበም

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስነ-ስርዓት ህግን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ አመልካች ባለመቅረቡና ተጠሪ ቀርበው መዝገቡ እንዲዘጋ በመጠየቃቸው ፍ/ቤቱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2) መሰረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች ለፍ/ቤቱ በታህሣሥ 14 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መዝገቡ እንደገና እንዲከፈትለት የቃል ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ያልቀረበበት ምክንያት በቂ ባለመሆኑ መዝገቡ ሊከፈት አይገባም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ትዕዛዞች ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታው የቃል ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ አመልካች ሳይቀርብ ተጠሪ ከቀረበ መዝገቡ ሊዘጋ የሚገባው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሰረት እንጂ በቁጥር 62(2) አይደለም፣ በቀነ-ቀጠሮው የቀረንበት ምክንያትም የብሔር ብሔረሰቦች በዓል የሚከበርበት ቀን ስለነበር መንገድ በመዘጋጋቱ አርፍደን ስለደረሰን ስለሆነ መዝገቡ እንዲከፈት ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡ አቤቱታውም ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፁሁፍ አቀርበዋል፡፡ መዝገቡም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች ቃል ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ሳይቀርብ ተጠሪ መቅረቡ አልተካደም፡፡ የባለጉዳዮች ወደ ፍ/ቤት መቅረብና አለመቅረብ የሚያስከትለውን ውጤት ምን እንደሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከቁጥር 65 እና ተከታዮች ባሉት ድነጋጌዎች ተዘርዝረው ተቀምጠዋል፡፡ በዚህ መሰረት ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ሳይቀርብ ተከሳሹ ቀርቦ ክሱን በከፊል ወይም በሙሉ ያመነ ከሆነ ሳመነው ጉዳይ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ለመስጠት እንደሚችልና ከካደ ደግሞ መዝገቡ እንደሚዘጋ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 ያመለክታል፡፡ በዚህ አንቀፅ ከሳሽና ተከሳሽ የሚለው

አነጋገር ይግባኝ ባይ መልስ ሰጪ እንደሚጨምር ከሥነ-ሥርዓቱ ድንጋጌ አንቀጽ 32(2) ሥር መመልከት ይቻላል፡፡ በሌሳ በኩል የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2) አግባብነት የሚኖረው ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ሁለቱም ተከራካሪዎች ያልቀረቡ ከሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ይግባኝ ባይ የነበረው አመልካች ሳይቀርብ ተጠሪ ቀርቧል፡፡ በዚህም ምክንያት አግባብነበት የሚኖረው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 እንጂ ቁጥር 69(2) አይደለም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2)ን መሰረት አድርጎ መዝገቡን መዝጋቱ ተገቢ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ ከአመልካች ጋር ሲከራከር የነበረ በመሆኑና ክርክር በሚሰማበት እለት አመልካች ባለመቅረቡ ተጠሪ መዝገቡ እንዲዘጋለት መጠየቁ ተጠቃሎ ሲታይ አቤቱታውን ያሳመነ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሌሳ በኩል አመልካች በቀነ-ቀጠሮው ያልቀረበው በበቂ ምክንያት ነው ቢልም ፍ/ቤቱ ምክንያቱን መዝኖ በቂ አይደለም የሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ የምክንያቱ በቂ መሆን አለመሆን ደግሞ የማስረጃ ምዘና እንጂ የህግ ክርክር ባለመሆኑ ለሰበር አቤቱታ የሚቀርብበት ነጥብ ነው ሲባል አይችልም፡፡ በአጠቃላይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መዝገቡን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሰረት መዝጋት ሲገባው በቁጥር 69(2) መሰረት መዝጋቱ ትክክል ባይሆንም መዝገቡ በመዘጋቱ ግን መሰረታዊ የህግ ስህተት ፈፅሟል ማለት አልተቻለም፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 39200 ህዳር 30 ቀን 2001 ዓ.ም እና ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጣቸው ትዕዛዞች ፀንተዋል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ